በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# መንፈሳዊው ሰው ማነው? - ክፍል 1

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን  አዳራሽ

በየሳምንቱ  ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሐምሌ ፲ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# መንፈሳዊው ሰው ማነው?  - ክፍል 1

***መግቢያ***

- ***መንፈሳዊነት እግዚአብሔርን የምናከብርበት የጠራ ሕይወት ሲሆን ይህም ሕይወት ለአማንያን ሰላምና ደስታን የሚያስገኝ ነው፡፡ የማንኛውም ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት በዚህ የሚደገፍ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ለዘላለማዊ ሕይወትም ሆነ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የማስፈለጋችንን ብቃት የሚወስነው በመንፈሳዊ እድገታችን ነውና፡፡***
- ***ይህም እድገት መንፈሳዊና በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ሊሆን የሚገባው እድገት ነው፡፡***
- ***ክርስቲያን መንፈሳዊ ሲሆን እርሱ ራሱ በአኗኗር መርሆውና በአርአያነቱ አስተማሪ ይሆናል እንጂ ምንም ምክር አያሻውም:: አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ ያልሆነውን ክርስቲያን በመምከር ብቻ ለውጥ ለማምጣት መሞከር ጊዜና ጉልበትን ማባከን ነው፤ እንደሚገባ ከመመላለስ ይልቅ ባልሆነ ነገር መነታረክ ይቀናዋልና፡፡***
- ***በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያድጉ ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን የሚወጡ ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን ተፈጥሮአዊ፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ በማለት በሦስት ደረጃ ከፍሎአቸው እናገኛለን፡፡***
- *‹‹ነገር ግን። ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ፥ እንዲህ እንናገራለን። መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።  በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።  እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም።  መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም።  **ለፍጥረታዊ ሰው** የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም።  **መንፈሳዊ ሰው** ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም።  እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።… እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ **የሥጋ ሰዎች እንደ** መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም።  ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤  ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?  አንዱ። እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ ሁለተኛውም። እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?››* ***ቀዳ ቆሮ 2:9 - 3:4::***

# መንፈሳዊው ሰው ማነው? - ክፍል 1

***መግቢያ***

- ***ሰዎች በዚህ የተለያየ ደረጃ የሚመደቡት የእግዚአብሔርን ነገር ለመቀበልና ለመረዳት ባላቸው ችሎታ ነው፤ የእግዚአብሔርንም ጥልቅ ነገር ለመረዳት የእግዚአብሔር እርዳታ ያስፈልገናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ስናደርግ የርሱን ነገር ማወቅ የምንችልበት ችሎታ እናገኛለን፤ ይህም በሁሉ የሚጠቅመን ታላቅ የችሎታ ምንጭ ነው፤ በራሳችን ልናውቃቸው የማንችላቸውን ነገሮች መንፈስ ቅዱስ ያሳውቀናልና፡፡***
- ***በጣም ግልጥ በሆኑ ነገሮች ብንከበብም እንኳ መንፈስ ቅዱስ ካልገለጠልን የእግዚአብሔርን ነገር ልንረዳ አንችልም፡፡***

1. ***ፍጥረታዊው ሰው***

- ‹‹ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም፡፡›› ***ቀዳ ቆሮ 2፡14፡፡*** ***በዚህ ገጸ ንባብ ፍጥረታዊው ሰው ባለማወቁ አልተገሰጸም፤ ይልቁኑ የፍጥረታዊውን ሰው ውሱንነት ያመለክተንና የውሱንነቱን ምክንያት ያስረዳናል፡፡***
- ***ፍጥረታዊው ሰው ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ አልተቀበለምና የተገለጡትን ነገሮች መረዳት አይችልም፡፡***
- ***የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸውን ቃላት ለማንበብ ቢችልም መንፈሳዊ ትርጉማቸውን ግን ሊረዳ አይችልም፤ እርሱ የተቀበለው በሥጋው ውስጥ ያለውን የሰው መንፈስ ነውና፡፡***
- ***ለፍጥረታዊው ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ገጸ ንባብ (ጥሬ ቃል) የሚሰጠውን ትርጉም መቀበል እንደሞኝነት ስለሆነ አያውቀውም አይቀበለውምም፡፡***
- ***የመለኮት ሥጋ መልበስ ነገር ለፍጥረታዊው ሰው በሚገባው መንገድ የተጻፈ ቢሆንም አንዳንዴ ስለ ነገሩ በርቱዕ እንደበትና ከልብ እየተናገረም እንኳየማያውቀው ሊሆን ይችላል፡፡*** ‹‹የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና፡፡… እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፡፡›› ***ቀዳ ቆሮ 1፡18 ፡፡***

1. ፍጥረታዊው ሰው...

# መንፈሳዊው ሰው ማነው? - ክፍል 1

- ለትያጥሮን ምዕመናን እንደ ተጻፈላቸው ሰይጣን በአስመሳይ ዘዴው የሚገልጣቸው ጥልቅ ነገሮችና ትምህርቶች *ራእ 2፡24፣ ቀዳጢሞ 4፡1-2፡፡* እግዚአብሔር የማይቀበላቸው ቢሆኑም በእውር ድንብሩ ለሚራመደው ‹‹ተፈጥሮአዊ ሰው›› እጅግ ምቹ ናቸው፡፡ የዘመናችንም የስህተት ሃይማኖቶችም የሚያረጋግጡልንም ይህንኑ ነው፡፡
- ፍጥረታዊው ሰው በሥጋዊ ጥበብ የሰለጠነ ቢሆንም ለእግዚአብሔር ቃል ግን የታወረ ነው፡፡ ሲጠየቅም ከመሠረታዊው የክርስትና ትምህርት የወጣ ነገር ይጠቅሳል፡፡
- በዓለማዊ ጥበብ ብቻ የሰለጠነ አእምሮ ካልተፈቀደለት በቀር የእግዚአብሔርን ነገር ሊረዳ አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነት ሰዎች የሚሰጡት አስተያየት ከፍተኛ ግምት እየተሰጠው አያሌ ክፉ ስህተቶችንና ነገሮችን በዓለማችን በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡
- ፍጥረታዊው ሰው በሥጋ ጥበቡና እውቀቱ በመመራት በመንፈስ ቅዱስ የሚገለጡ ነገሮችን እንደ ‹‹ሞኝነት›› ይቆጥራቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሳይንሳዊ እውቀት የእግዚአብሔርን መንፈስ ነገር ፈጽሞ ሊተካ አይችልም፡፡
- በጥምቀት ከቤተ ክርስቲያን ያልተወለደ መንፈስ ቅዱስንም ያልታደለው ፍጥረታዊው ሰው የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ዋጋ ቢስ ይቆጥረዋል፤ የዘመናችን አንዳንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ስህተትም ይኸው ነው፡፡
- በአንድ ወይም በብዙ ሰብአዊ የእውቀት ዘርፎች ጥልቅ እውቀት ያለው አስተማሪ፣ ሰባኪ ወይም ተማሪ በዚያ እውቀቱ የተነሳ ተመጣጣኝ በሆነ ችሎታ መንፈሳዊ ነገሮችን ማስተዋል ይችላል የሚል አጠቃላይ አቋም መያዝ ታላቅ ስህተት ነው፤ ለፍጥረታዊው ሰው እግዚአብሔር እውን አይደለምና ‹‹በአስተሳሰቡም እግዚአብሔር የለም፡፡››
- ፍጠረረታዊው ሰው ከተፈጥሮ በላይ የሆነበትን ነገር ወዲያ እንዲጥል የሚያስገድድ ጭንቅና ሽክም አለበት፡፡ ስለ ሥነ ፍጥረትም መሠረት የለሽ የሆነውን የአዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብ ያራምዳል፡፡ ያላመኑትና ያልዳኑት ሁሉ ያለ ልዩነት ‹‹ፍጥረታውያን›› ተብለዋል፡፡
- በጥምቀት የተወለደው ግን እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪና ጌታ መሆኑን ያምናል፤ በዚህም እርካታና እረፍት ይሰማዋል፤ እግዚአብሔር ለርሱ እውነት ነውና፡፡

# መንፈሳዊው ሰው ማነው? - ክፍል 1

2. ***ሥጋዊው ሰው***

- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ *ሥጋዊው* ሰው *ያመነና* የተጠመቀ እንደሆነ በመግለጥ ‹‹ እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን? አንዱ። እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ ሁለተኛውም። እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን? ›› ***ቀዳ ቆሮ 3:1-4::*** በማለት አንዳንድ ክርስቲያኖች *ሥጋውያን* የተባሉት የቃሉን ወተት እንጂ ጠንካራውን ምግብ መመገብ ስለማይችሉ ነው::
- እነዚህ ክርስቲያኖች ለቅንዓት፣ ለክርክርና ለመከፋፈል በመሸነፍ ከእውነተኞቹ እንደሚጠበቀው በመንፈስ፣ በፍቅር፣ የመንፈስን አንድነት በመጠበቅ ከመመላለስ ይልቅ እንደ *ሥጋ* ይመላለሳሉ:: ***ገላ 5:16፣ ኤፌ 5:2፣ ኤፌ 4:3::***
- *ያመኑና* የተጠመቁ ቢሆኑም የሚመላለሱት ‹‹እንደዚህች ዓለም አሳብ›› ነው:: *ሥጋቸውም* ስለሚገዛቸው *ሥጋውያን* ናቸው:: ***ሮሜ 7:14::***
- ካልዳኑት ወገን የሆኑ *ሥጋውያን* ቢኖሩም *ሥጋውያን* የሆኑት በውስጣቸው ባለ *ሥጋዊ* ሕይወት ነው::
- *ሥጋዊው* ሰው የተማረውን ቃል ወፎች መጥተው ስለሚለቅሙት የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ማቆየት አይችልም:: በእውነተኛው መንፈሳዊ ምግብ ላይ ብዙ ጊዜ ስለሚያሳልፍ ተጠቃሚ ከመሆን ይልቅ በአማንያን መካከል መለያየትን ለሚፈጥሩት ለቅንዓትና ለክርክር ተሸናፊ ይሆናል:: ይህም የክርስቲያኖችን አንድነትና ፍቅር የሚያፈርስ ነው:: በዘመነ ሐዋርያት የነበሩት ‹‹ጳውሎሳውያን››፣ ‹‹ኬፋውያን››፣ ‹‹አጵሎሳውያንና›› ‹‹ክርስቶሳውያንም›› እንዲህ ያሉ ነበሩ:: ***ቀዳ ቆሮ 1:12::***
- እነዚህም በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተቀፈቀፉ ቡድኖች ሲሆኑ መጨረሻቸውም ተሻኳች ቡድኖችን መፍጠር ነው:: ለአንድ ክርስቲያን በቡድናዊነት መመካት ‹‹የሕጻን ጨዋታ›› ከመሆኑም በላይ የፍቅሩን ጎዶሎነትን ያሳያል:: ***ቀዳ ዮሐ 4:8::*** ፍቅር ቢኖር ግን መከፋፈል ይጠፋል ጥፋትም ይወገዳል::

# መንፈሳዊው ሰው ማነው? - ክፍል 1

2. <u>ሥጋዊው ሰው</u>

- ‹‹ሥጋዊውን›› ክርስቲያን ‹‹ከፍጥረታዊው›› ሰው ጋር በአንድ መደዳ የሚያሰልፈው ሌላው ባሕርይ አኗኗሩ ነው፡፡ ‹‹ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?›› ***<u>ቀዳ ቆሮ 3፡3፡፡</u>***
- የሥጋዊ ክርስቲያኖች ግቦችና ምኞቶች እንደ ‹‹ፍጥረታዊው›› ሰው መንፈሳዊ ባልሆኑ ነገሮች ተከማችቶ መኖር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ግን ‹‹ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።›› ***<u>ገላ 5፡16፡፡</u>*** ይለናል፡፡

3. <u>መንፈሳዊው ሰው</u>

- ‹‹… መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም።›› ***<u>ቀዳ ቆሮ 2፡9-15</u>*** እንዳለ በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠውን የሚያውቅ ነው፡፡ የተገለጠለትም በመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡
- ማንም ስለ ማያውቀው የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገሮች ያውቁ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጣቸው ናቸው፡፡
- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙት ቃላት ውስጥ ተደብቆ የሚገኘው መንፈሳዊ ይዘትና ምስጢር (ትርጉም) የተረዳና የሚያስረዳ ነው፡፡
- እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሚኖርና የሚመላለስ ነው፡፡
- በሰው ሕይወት ውስጥ ሁለት ታላላቅ መንፈሳዊ ለውጦች አሉ እነዚህም ከፍጥረታዊ ሰውነትና ከሥጋዊ ሰውነት ወደ መንፈሳዊ ሰውነት መለወጥ ናቸው፡፡
- የጠርሴሱ ሳውል የጌታችንንም አዳኝነትና አምላክነት ካመነና ከተጠመቀ በኋላ ከክርስትና ሕይወት ዘወር አላለም፡፡
- ብዙ ክርስቲያኖች ግን ወደ ሥጋዊነት መመለሳቸው ተጽፎልናል መፍትሔውም ከሥጋዊነት ወደ መንፈሳዊነት መሸጋገር እንደሆነም ተገልጾልናል፡፡ ‹‹ የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና። ››እንዳለ ***<u>ቀዳ ጴጥ 4፡3፡፡</u>***
- መንፈሳዊው ሰው በሕይወቱ፣ በአምልኮቱም ሆነ በአገልግሎቱ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሆነ የእግዚአብሔርን (የመለኮትን) ዕቅድ ሲፈጽምና ሲያስፈጽም ይኖራል፡፡

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org